# የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ

# ተከራዮች: መብቶችዎን ይወቁ!

## የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ ምንድን ነው?

ወደ አዲስ አፓርታማ ተከራይተው ሲገቡ፣ አብዛኛዎቹ አከራዮች **ከመጀመሪያው ወር የቤት ኪራይ** በተጨማሪ **የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ** ይጠይቁዎታል። አንዳንድ አከራዮችም **የመጨረሻውን ወር ኪራይ** አስቀድመው ይጠይቃሉ። ስለዋስትና ማስያዣዎች ማወቅ ያለቦት ተጨማሪ ነገሮች:-

የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ አብዛኛውን ጊዜ **ከአንድ ወር የቤት ኪራይ ዋጋ** ጋር እኩል ነው፣ ነገር ግን አንድ አከራይ ለሚያስከፍለው የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ **ገደብ የለውም**።

አከራዮች የዋስትና ማስያዣ ገንዘቡን **በተለየ የባንክ አካውንት** ማስቀመጥ አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን ቤቱን ለቀው በሚወጡበት ጊዜ ገንዘቡን ማቆየት አይችሉም።

አከራዩ ገንዘቡን ማቆየት የሚችለው **ያልተከፈለ ኪራይ** ወይም **የአገልግሎቶች ክፍያ** ካሉ ለመክፈል እንዲሁም በእርስዎ ወይም በእንግዳዎ ምክንያት ቤቱ ላይ የደረሰ **ጉዳት** ካለ **ለማስጠገን ብቻ** ነው።

**አንዳንድ አከራዮች ከዋስትና ማስያዣ ገንዘብ ይልቅ ተመላሽ የማይደረግ የውል ክፍያ ያስከፍላሉ። የኪራይ ውልዎን በመመልከት የከፈሉት የተቀማጭ ገንዘብ ተመላሽ የሚደረግ መሆኑን ያረጋግጡ።**

## የማስያዣ ገንዘቡ እንደሚመለስልኝ እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?



1. ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ **በአራት ቀናት** ውስጥ ከአከራይዎ ጋር **የቤት ውስጥ ቅኝት** ያድርጉ።
2. አከራዮ የሚጠገኑ ወይም ክፍያ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ዝርዝር ሊያዘጋጅ ይችላል።**በዝርዝሩ ላይ በተጠቀሱት ነገሮች በሙሉ ካልተስማሙ ይህንን አይፈርሙ**።
   ሀ. በዝርዝሩ ላይ የማይስማሙበት **ማንኛውም** ነገር ካለ ከተጠቀሰው ላይ **አከራካሪ** ይበሉበትና **ስምዎን ጽፈው ይፈርሙ**። ትክክል ነው ብለው የሚያስቡትን **የራሶት ዝርዝር** አዘጋጅተው ይፈርሙበት።
   ለ. የራሶትን ዝርዝር **በሁለት ኮፒ** ያዘጋጁ። ፊርማዎትንና ቀኑን በሁለቱም ላይ ጽፈውበት **አንዱን ለአከራዮ ይስጡ**።
3. ለአከራዮት የዋስትና ክፍያው እንዲላክበት የሚፈልጉትን **አዲስ አድራሻ** ይስጡ።

አከራዮት **ማንኛውም የሚጠገኑ እና የሚከፈሉ ወጪዎችን ማጠቃለያ በጽሑፍ አዘጋጅቶ ቤቱን በለቀቁ በ30 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ** ሊሰጡት ይገባል። ቤቱ ላይ ምንም አይነት ጉዳት ካላደረሱ እና ለአከራዮት ያለቦትን ሂሳብ በሙሉ ከከፈሉ **አከራዩ የከፈሉትን የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ ሊመልስሎት ይገባል**።

**አከራዮ የዋስትናውን ገንዘብ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ በህግ መጠየቅ ይችላሉ። ከህግ ባለሙያ ጋር ለመነጋገር እና ሂደቱን ለመረዳት help4tn.orgን ይጎብኙ።**

## ቤቱን በምለቅበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብኝ?

### ቤቱን ከመልቀቆ ከ60ቀናት በፊት...

- **የኪራይ ውሎትን በማንበብ** በሚለቁበት ጊዜ ማድረግ ያለቦትን ነገር ይመልከቱ።
- ለአከራዮት ቤቱን መልቀቅ እንደሚፈልጉ **በኢሜል ያሳውቁ**። አዲሱን አድራሻዎትን ይስጡ። የከፈሉትን የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ እንዲመልስ ይጠይቁ፤ እንዲሁም የቤት ውስጥ ቅኝት እና ግምገማ ለማድረግ ይጠይቁ።

### ከመጨረሻ ቀኖት በፊት ...

- ያለቦትን ክፍያ ይክፈሉ፣ እንደ ቤት ኪራይ ወይም የአገልግሎቶች ክፍያ
- **እቃዎትን በቻሉት ፍጥነት ይሰብስቡ። ቦታውን ያጽዱ አዋራውን ያራግፉ። በቤቱ ውስጥ ወይም አካባቢ ቆሻሻ አይተዉ። የልብስ ማስቀመጫ፣ ኮርኒስ፣ ከመሬት በታች ያለውን መጋዘን እና መኪና ማቆሚያውን ይፈትሹ።**

### በሚለቁበት ቀን ...

- **ያሎትን ንብረቶች በሙሉ** ተከራይተውት ከነበረው ቦታ ያስወጡ። ያስቀሩት ነገር ካለ እርሱን ለማስነሳት ክፍያ ሊጠየቁ ይችላሉ።
- የለቀቁትን ቤት **ፎቶ ያንሱ እንዲሁም ቪዲዮ ይቅረጹ**።
- ቁልፎን **ይመልሱ**።

**SECURITY DEPOSITS**

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837-የቤት

AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460

conexión américas (615) 701-7957

Nashville Hispanic Bar Association

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ክልል ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክርን አይመሰርትም፤ ለመመስረት የታሰበም አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎት ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድ ቢሮ በ1-800-238-1443 ወይም የናሽቪል የሂስፓኒክ ባር ማህበርን በ1-615-701-7957 ይደውሉ።

በ5/23 ተሻሽሏል።